# <u>የወያኔ “ተቃዋሚ” ፖለቲካ ድርጅቶች</u>
# <u>የአስራ አምስት ዓመት “ትግል”!?</u>

**በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት**
**የድጋፍ ኮሚቴ**

7/6/2006

<u>የወያኔ “ተቃዋሚ” ፖለቲካ ድርጅቶች የአስራ አምስት ዓመት “ትግል” ?!</u>

ወያኔ ከአሁን/አሁን፣ ከዛሬ/ ነገ፣ ከዓመት/ ዓመት ሊሰበር/ ሊወድቅ፣ ሊነቀል/ ሊቀበር ነው እየተባለ ሲጠበቅ እነሆ አስራ አምስት ዓመት አልፏል።

በአንጻሩ ደግሞ የወያኔ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች ለአስራ አምስት ዓመት ያካሄዱት ትግል ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ የሚችል ሆኖ አልተገኘም።

እንግዲህ እዚህ ላይ በግድ መነሳትና መመለስ ያለበት ጥያቄ <u>ወያኔ የሚቃወሙትንና የሚታገሉትን የፖለቲካ ድርጅቶችና ኃይሎች ሁሉ አሸንፎና አንበርክኮ በመንግሥት ሥልጣን ላይ መቆየትና መቀጠል የቻለው ለምንድር ነው</u>? ጥያቄውን ከዚህም ይበልጥ ግልጥልጥ/ፍርጥርጥ አድርጎ ለማቅረብ <u>ወያኔን ያጠነከረው/ ተቃዋሚዎቹን ያዳከመው ምንድር ነው</u>?

የማንኛውም ዓይነት መንግሥት ጥንካሬ በሁለት ዓበይት መስፈርቶች ይመዘናል። እነርሱም፣

1. በሕዝብ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነትና ተፈላጊነት አለው?
2. የማስገደጃ ኃይሉ (ጉልበቱ = ወታደር፣ ፖሊስ፣ ስለላ ወዘተ) ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ነው።

የወያኔ መንግሥት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ (እስከአሁን ወቅት) በሕዝብ የተጠላና የተተፋ ስርዓት ነው። “የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ሂደት” ፣ “የብሔረሰቦች ነፃነትና እኩልነት” በሚል መልካም ስምና ማደነጋገሪያ ተሸፋፍኖ የነበረው የወያኔ ክፉ ገላ ተራቁቶና ተገልቦ ለአገርና ለዓለም የሚታይና የሚሸትት ሆኗል። በተለይም ከግንቦት 97 ምርጫ ወዲህ ሕዝብን መረሸን፣ ማሳደድና ማሰር ዋናውና የማያቋርጥ ተግባሩ እንደሆነ ቀጥሏል። “ሕጋዊ”/ “ዴሞክራሲያዊ” “አብዮታዊ” … ወዘተ እያለ በማፈራረቅና በማከታተል ያዠጐደጐዳቸው የነበሩት መቅጠፊያዎቹና ማታለያዎቹ ሁሉ ረክሰዋል። ወያኔ በባእዳን ኃይሎች ተረድቶና ተመክሮ የነርሱንና የቡድኑን ጥቅም ለማስጠበቅ የኢትዮጵያን ሕዝብ መብትና ነፃነት፣ የአገሪቷንም የተፈጥሮ ሀብትና ንብረት የቀማ የጐጠኞችና የነፍሰ ገዳዮች ስብስብ እንደሆነ የማያውቅ የለም።

ወያኔንና ስርዓቱን ከአገራችን ሁለንተናዊ (ወቅታዊና ዘላቂ) አቅጣጫና ዘርፍ በዝርዝርና በተደጋጋሚ ተብራርቶ ተገልጿል። በአጭሩ የወያኔ ስርዓት ከአገራችን ሁለንተናዊ ጥቃትና ጥፋት ተለይቶ ሊታይ የማይችል ሆኗል። በዛሬ ጊዜ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ (ሕዝቦች) ዋና ጠላት ነው። በአገር ወዳጅነትና አጋርነት የሚመለከተው ከአለ ያው የወያኔ ወዳጅና የአገር ጠላት ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው።

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በተለይ ከግንቦቱ ምርጫ ወዲህ፣ የወያኔ መንግሥት ተደግፎ የቆመው በነፍሰ-ገዳይ መዋቅሮቹ (የወታደር፣ የስለላ የፖሊስ ድርጅቶቹ) እና በገንዘብ፣ በፖለቲካ ረድተው በሰማይና በምድር እየመሩ አዲስ አበባ ድረስ በሸኙትና

ምኒልክ ቤተ መንግሥት ባስገቡት የአውሮፓና የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥቶች ናቸው። ታዲያ የወያኔ መንግሥት በማስገደጃና በማፈኛ መዋቅሮችና በባእዳን ኃይሎች ከተደገፈ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት የሚወገድበትና የሚገለልበት ሁኔታ ሊኖርና ሊፈጠር አይችልም ማለት ነውን?

ወያኔ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑ የማያወዛግብ ከሆነ፣ በአንድነትና በአንድ ልብ ተነስቶ አስፈላጊ የሚሆነውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ ወያኔን ከማስወገድ የሚያስቀረው ማንና ምን ዓይነት ኃይል ሊኖር ነው?

የወያኔ መንግሥት የሰረቀውን የምርጫ ሳጥን ድምጽ ለማስመለስ በሰላማዊ መንገድና በቁርጠኝነት ቀፎው እንደተነካበት ንብ መብቱን ለማስከበር ከአደባባይ ወጥቶ በየከተማውና በየባላገሩ ተሰለፈ። "ድምጼ ይከበር" ብሎ ጮኸ። የተሰጠው መልስ የመድፍ የመትረየስ ጥይት ሆነ። <u>በእግሩ /በሕይወት የወጣው ሁሉ ሬሳ ሆኖ ተመለሰ!!</u>

ሳይፈራና ሳይደነግጥ ጥያቄውን እየደጋገመ ከመጠየቅ (ከመሰለፍ) እና በባዶ እጁ በድንጋይና በዱላ ከጠላቱ ታንከኛና እግረኛ ወታደር ጋር ያካሄደው ትግልና መስዋዕትነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና እየመረረ ሄደ። በዚያው ልክ የጠላት ደጀን ተብረከረከ። ሕዝብ ወያኔን ከምኒልክ ቤተመንግሥት ሳያስወጣ እንደማይመለስ እውን እየሆነ መጣ።

እንግዲያውስ ወያኔ ደምኖና ጐርፎ በመጣው የሕዝብ አመጽና ቁጣ ተጠራርጐ ያልጠፋበት ምክንያት ምንድር ነው?

<u>ለመላው ያገሪቷ ሕዝብ መብትና ጥቅም፣ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት፣ ለብሔረሰቦች እኩልነትና ለአገር አንድነት የቆመ የፖለቲካ ንቅናቄና ድርጅት ባለመኖሩ ነው። የዚህ ዓይነት ድርጅት ኖሮ የሕዝብን ትግል ማገዝ (መስመር በማስያዝ፣ ስልት በመንደፍ፣ የፕሮፓጋንዳ ዓይነት በመምረጥ ወዘተ) ባለመቻሉ ነው።</u>

እንዲያውም ሕዝቡ በራሱ የፖለቲካ ንቃት ተቀስቅሶና ተቆስቁሶ በመነሳት የወሰደውን ቆራጥ እርምጃ ሁሉ በአሉታዊነት የተረጐሙበት አልታጡም?! ያውም "የነርሱን" አቋምና ድምጽ ("ምርጫው ተጭበረበረ/ የሕዝብ ድምጽ ይከበር") ደግፎ ስላስተጋባ ! በቆመጥ ሲቀጠቀጥ በመድፍና በመትረየስ ሲረግፍ ድንጋይ ስለወረወረ "<u>በሽብርተኝነት" እና "በነውጠኛነት</u>" አወገዙት?! እነማንና የትኞቹ ፓርቲዎች እንደሆኑ የማያውቅ ከአለ፣ የዚያን ሰሞን ጋዜጦችና መግለጫዎች… ዞር ብሎ ማየትና ማስታወስ ነው። ሕዝቡ ግን በያለበት የተቃውሞ ሰልፉንና ትግሉን አፋፍሞ ቀጠለ እንጂ በወያኔ አፈናና ጭፍጨፋ ተገድቦ አልቆመም። እስራቱም እልቂቱም ቀጠለ።

የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች (በተለይም ሕብረትና ቅንጅት) ከሙያ ማኅበሮች፣ ከሲቪኩ ማኅበረሰብ ስብስቦችና ቡድኖች ጋር በመተባበር የሕዝቡን ተቃውሞ ለማቀነባበርና የወያኔን አረመኔነትና አሸባሪነት ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ (በተለይም ለወያኔ ጌቶችና መንግሥቶች) ለማጋለጥ ተስማምተው ወሰኑ።

መስከረም 22 ቀን 1997 ዓ.ም. አገር አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ እንደሚደረግ በይፋ ተነገረ። ወያኔ ብርክ ያዘው። ሰማይና ምድር ጠበበው።

ለምሳሌ፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ፣ “ቁጥራችን 4 ሚሊዮን ይደርሳል። ምኒልክ ቤተመንግሥት እስክንደርስ የጠላት ጦር አንድ ሚሊዮናችንን ማስተኛት ይችል ይሆናል። የምንቀረው 3 ሚሊዮናችን ወያኔን ከሕዝብ ቤት (ከቤተመንግሥት) አባርረን፤ ቀምቶ ከተቀመጠበት የሕዝብ ወንበር አሽቀንጥረን እናስወጠዋለን፤ እንጥለዋለን ነበር ያለው!! ወያኔ ራሱን ሕጋዊ፣ ሕግ አስጠባቂና ሰላማዊ አሰኝቶ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን በአመፀኝነትና በሕግ አፍራሽነት ከሰሰ/ወነጀለ። የታሰበው ሰላማዊ ሰልፍ ከተደረገ በኃይል ተጠቅሞ ሕግ እንደሚያስከብር አስታወቀ።

የምዕራብ አውሮፓና የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥታት ወኪሎችና ልዑካኖች የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ያቀዱትን ሰላማዊ ሰልፍ እንዲሰርዙ ማስጠንቀቂያና ትዕዛዝ አስተላለፉ። ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ከወያኔ ጋር ተቀራርበው፣ ተወያይተውና ተግባብተው እየሰሩ ተቃውሚቸውን በፍርድ ቤት እንዲቀጥሉ የሚል የማስታረቂያ (የማስፈራሪያ) አሳብ አቀረቡ! በአቋማቸው እስከመጨረሻው ፀንተው የቆዩት የቅንጅት አመራሮች ታሰሩ።

አገር ቤት ከነበሩት የሕብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል፣ የደቡብ ሕብረትና የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ መሪዎች (በየነ ጴጥሮስና መረራ ጉዲና) የወያኔን ፓርላማ ተቀላቀሉ። እነ ልደቱ አያሌውም እነርሱን ተከተሉ። ከሕዝብ ደጀን ሸሽተው ወደ ጠላት ደጀን ገቡ። ተሟሙቆ፣ ተፋፍሞና ተጋግሎ በመቀጣጠል ላይ በነበረው የሕዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ጨመሩ።

በአጭሩ፣ እስከ ግንቦቱ (1997) ምርጫ ድረስ በተቃዋሚነት የወል ስም ሲጠሩ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሸረካከቱ። ተከፈሉ። ሚናቸውን ለዩ።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥያቄ በተቃዋሚነት የወል ስም ሲጠሩ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ከወያኔ ጋር የነበራቸው/ያላቸው አንድነትና ልዩነት ምንድር ነው? በሌላ አነጋገር፣ እነዚህ ድርጅቶች ሁሉ ወያኔን እንዲቃወሙ ያነሳሳቸው አንድ ዓይነት ወይስ የተለያየ ዓይነት ምክንያት ነበር/ነው?

ይህ ጥያቄ ሊመለስ የሚችለው የድርጅቶቹን ፕሮግራም በማየት ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ በሚወስዷቸው አቋሞችና እርምጃዎች ጭምር እንጂ።

ከዚህ ግንዛቤ ተነስተን እነዚህን ድርጅቶች ስናወዳድር፣ አንዳንዶቹ ወያኔ ተወግዶ የቡድናቸውን መንግሥትና ስልጣን ማቋቋም የሚፈልጉ ሆነው እናገኛቸዋለን። የተቃውሟቸው ግብ ወያኔን መተካት ነው።

በወያኔ እግር ተተክተው የቡድናቸውን መንግሥትና ስልጣን ከማጠናከር ውጪ የሚፈልጉትም የሚያዩትም የላቸውም። ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመመስረትና ሕዝባዊ ሕገ መንግሥት የማርቀቅና የማጽደቅ ጥያቄ አንገብጋቢና ተቀዳሚ ጉዳያቸው አይደለም። በበላይነት የመንግሥት ስልጣን መያዝ ባይሆንላቸው እንኳን ከወያኔ ጋር

ክፍያና ድርሻ እንዲኖራቸው ይመኛሉ። ለምሳሌ ቅንጅት የወያኔን ሕገ መንግሥት ተቀብሎ በራሱ የፖለቲካ ኘሮግራም ተወዳድሮ ወያኔን መተካት (ካሸነፈ)፣ ምርጫው በትክክል ተካሂዶ ከተሸነፈ (ቅንጅት) ከወያኔ መንግሥት (ፓርላማ) ጋር ሆኖ መስራት በሚል መመሪያ ነበር ወደ ምርጫ የገባው።

ሕብረቱ ግን ወያኔን የአገርና የሕዝብ ዋና ጠላት አድርጐ ይፈርጀዋል። ወያኔና አምባ ገነናዊ (ሁሉንም የመንግሥት ሥልጣን ወደ አንድ ፓርቲ እጅ የሚያስገባ) ሕገ መንግሥቱ በሕዝብ ላይ የተጫኑ እንጂ በሕዝብ የተመረጡና የተፈቀዱ አይደሉም። ስለዚህ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመስረትና የመድበለ ፓርቲ ልምድ ስር እንዲሰድድ ለማድረግ ወያኔ በቅድሚያ መወገድ አለበት። በሽግግር ወቅትና መንግሥት አማካይነት በመድበለ ፓርቲ ላይ ወደ ተመሰረተ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውድድር መሸጋገር ይቻላል/ ይሻላል ብሎ ያምናል።

“የፖለቲካ መብት ምንጭና ባለቤት ሕዝብ ነው”፤ የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ለሚቀበል ሁሉ ይህ አባባል ሊታበልና ሊታለፍ የማይችል ነው።

ኦነግን የመሳሰሉ ድርጅቶች ደግሞ ከወያኔ ጋር መሠረታዊ የፖለቲካ ፍልስፍና (አመለካከት) ልዩነት የላቸውም። የወያኔን ሕገ መንግሥት እጅግ አድርገው ይደግፋሉ። በዋናነት (ከሻቢያና ከወያኔ ጋር ሆነው) የአሁኑን ሕገ መንግሥት ካረቀቁት ቡድኖች አንዱ ኦነግ እንደነበር የሚታወስ ነው። ኦነግ ከወያኔ ጋር የተቀያየመው በሹመት፣ በስልጣን ክፍፍልና ድርሻ ላይ ብቻ ነው።

ኦነግ ያረቀቀውን ሕገ መንግሥት የሚቃወምበት ምክንያት የለውም። የአሁኑ ሕገ መንግሥት ተሽሮ በሌላ ሕገ መንግሥት መተካቱን ይቃወማል። የኦነግ የፖለቲካ ኘሮግራም የሚያርፈው “ኦሮሚያን” በማስገንጠልና “ነፃ አገር” በመመስረት ጥያቄ ላይ ነው። ለዚህም ነው የወያኔ ሕገ መንግሥትና የክልል ፖሊሲው ተጠብቆ እንዲቆይ አጥብቆ የሚታገለው።

ስለዚህ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ከወያኔ ጋር ያላቸው ቅራኔና የድሕረ ወያኔ የፖለቲካ ዓላማቸው የተለያየና የማይዋዋጥ ሆኖ በመገኘቱና በመቆየቱ እስካሁን በአንድ የጋራ ኘሮግራም ዙሪያ ተሰልፈው ወያኔን መታገልና ማስወገድ አልቻሉም/ አልፈለጉም።

በድህረ ወያኔ ሂደት ላይ የፖለቲካ ዓላማቸው ግብ የሚመታና ምኞታቸው የሚሳካ ካልመሰላቸው ይህንኑ አሸባሪ መንግሥት ለማስወገድ በሚደረገው ትግልና ጥረት ተግተውና ወድደው ከመሳተፍ ይቆጠባሉ። እንቅፋትም ይፈጥራሉ። ራሳቸውም እንቅፋት ይሆናሉ።

እናም ወያኔ ተዳክሞና ዘምሞ መሬት ሊነካ በተቃረበባቸው ወቅቶች ሁሉ፣ ደግፈውና አቃንተው ወደነበረበት ተመልሶ እንዲቆም ሲረዱትና ሲያጠናክሩት ይታያሉ።

## መደምደሚያ

አብዛኛዎቹ የወያኔ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ ወያኔን የሚቃወሙትና የሚታገሉት ለአገሪቷ ሕዝብ ሁሉ የሚበጅ የአስተዳደር ስርዓት ለመመስረት አይደለም። ይህ ዓይነቱን ግብ ለመምታት ተባብረውና ተጋግዘው የአገሪቷን ችግር በአንድነት ለመፍታት የተሰለፉ ኃይሎች ሆነው አይታዩም።

አብዛኛዎቹ የተወሰኑ የአገሪቷ ክፍሎችንና ብሔረሰቦችን እንወክላለን የሚሉ ናቸው። እንወክለዋለን በሚሉት ሕዝብና አካባቢ ስም የቡድናቸውን የስልጣን ድርሻ ለማሳደግና ለማሳበጥ ከሚያደርጉት ጥረትና ትግል ውጪ መሰረታዊ በሆኑ የወል (ሁሉ-ገብ ሁሉን-ነክ) ጥያቄዎች ላይ አያተኩሩም። ዓላማቸውና ጥረታቸው ውሱን፣ ቡድናዊና ጠባብ ነው።

በአጭሩ ዓላማቸው ከወያኔም ጋር ሆነ ከማንኛውም ሌላ አምባገነን ኃይል ጋር ሥልጣን ከመካፈል ወይም ራሳቸው በበላይነት የመንግሥት ሥልጣን ከመያዝ ፍላጐትና ምኞት የሚዘልል አይደለም።

ከወያኔ ጋር መሰረታዊ የሆነ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት የላቸውም። ስለሆነም እነርሱም የሚያመልኩት የወያኔ ጣኦቶችንና ጌቶችን ነው። የሰሜን አሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ ዓለም ተቆጣጣሪ መንግሥቶችን ነው። ወያኔን ለመተካትና ባለተራ ለመሆን አሰፍስፈውና አዘውትረው ዋሽንግተንን፣ ለንደንን፣ ወዘተ ደጅ የሚጠኑትም በዚሁ ምክንያት ነው። ወያኔን የሚቃወሙትና የሚታገሉት እኛ ይበልጥ አስተማማኝ የሆንና የቀለጠፈ አገልግሎት ማበርከት እንችላለን በማለት ነው።

አሽከሮችና ባሪያዎች ጌታቸውን ለማስደሰት የሚያሳዩትና የሚያሰሙት ውድድርና ፉክክር ነው!

ከላይ የተጠቀሱት የሰሜን አሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ የዓለም ተቆጣጣሪ መንግሥቶች ከክልሎቻቸው ውጪ በሚገኙ አገሮች (በተለይም እጅግ ወደኋላ በቀሩና ሦስተኛው ዓለም በሚል የጥቅል ስም የሚጠቀሱት አገሮች) ውስጥ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትም ሆነ የኤኮኖሚ ዕድገት እንዲኖርና ስር እንዲሰድድ አይፈልጉም።

በተለይ በአሁኑ የታሪክ ወቅት እነዚህ ኃያላን የዓለም ተቆጣጣሪ መንግሥቶች፣ የቀድሞው ሶቪየት ዩኒየንን የመሳሰሉ ተወዳዳሪና ተቀናቃኝ ባላንጣዎች ስለሌሉዋቸው (ስለሌሉባቸው) በሦስተኛ ዓለም አገሮችና ሕዝቦች ላይ የሚያካሂዱት ዝርፊያ፣ ቅሚያና ብዝበዛ ገደብ የለሽና መረን የለቀቀ ሆኗል።

በተጠቃለለና በአጠረ አነጋገር - በአሁኑ ወቅት ከምን ጊዜም ይበልጥ የሦስተኛ ዓለም አገሮች የተፈጥሮ ሀብት፣ ኤኮኖሚና አስተዳደር በሰሜን አሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ ከበርቴዎች ይዞታና ቁጥጥር ስር ወድቋል። በዚያው መጠን የሦስተኛ ዓለም አገሮችና ሕዝቦች ሁለንተናዊ አቅምና ነፃነት ፍጹም እየተሟጠጠና እየጠፋ በመሄድ ላይ ይገኛል።

በሦስተኛ ዓለም ውስጥ የእርሻም ሆነ የኢንዱስትሪ አገር በቀል ምርቶች ተዳክመውና ተመናምነው እየጠፉ ያላንዳች ገደብ ከውጭ በሚገቡ ሸቀጦች እየተተኩ በመሄድ ላይ ናቸው። የአገር ውስጥ ምርቶች በጥራትም ሆነ በዋጋ የውጭ ምርቶችን መወዳደርና መቋቋም የሚችሉ አይደሉምና። ለብዙ ሺህ ዘመናት ከየአገሩ አፈርና አየር ጋር ተስማምተውና ተላምደው እስከዛሬ የዘለቁትን የቤት እንስሳትና የምግብ አዝርዕት በሰው ሰራሽ የተክል ዘሮችና (genetically modified seeds) ዲቃላ ላሞች (የፈረንጅ ላሞች) እንዲተኩ ጥረት ያደርጋሉ።

በመንግሥት ወጪ ተቋቁመው በአነስተኛ ክፍያና ዋጋ ለሕዝብ ደህንነትና አገልግሎት እንዲውሉ ተመስርተው የነበሩ ተቋሞች ሁሉ (ትምህርት ቤቶች፣ ሐኪም ቤቶች፣ የውሃና የመብራት አገልግሎት ማዳረሻና ማሰሪጫዎች ወዘተ) በነዚሁ ባዕዳን መንግሥቶችና ከበርቴዎች ትዕዛዝ ወደ ግል ይዞታ ይቀየራሉ። በነዚህ ዓይነት የግል ተቋሞች መገልገል የሚችሉ የከፍተኛ ንብረትና ገቢ ባለቤቶች ብቻ ናቸው።

በሦስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ አብዛኛው የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚተዳደረው ለመንግሥት ተቀጥሮ በመሥራት ነው። ዋነኛው ሥራ ሰጪና ቀጣሪ መንግሥት ነው።

የዓለም ተቆጣጣሪ ከበርቴዎች (በመንግሥቶቻቸው አማካይነትና መሳሪያነት) በሦስተኛ ዓለም ውስጥ በመንግሥት ተቀጥሮ የሚሰራው ሰው ቁጥር እጅግ እንዲቀነስ ይመክራሉ። ያዝዛሉ።

የሦስተኛ ዓለም አገሮች ያለ ገደብ የውጭ ምርቶች እንዲገቡ ካልፈቀዱ፣ በመንግሥት ቁጥጥርና ይዞታ ሥር የሚገኙ ንብረቶችና ተቋሞች ወደ ግል ባለቤትነት ይዞታ እንዲቀየሩ ካላደረጉ ከዓለም ተቆጣጣሪ ከበርቴዎች "<u>እርዳታና ብድር</u>" አያገኙም። የዓለም ገንዘብ ድርጅት (IMF) እና የዓለም ባንክ (World Bank) "እርዳታና ብድር" አይሰጡም (ለሦስተኛ ዓለም መንግሥቶች)። የሦስተኛ ዓለም አገሮች ከተጠቀሱት የዓለም ከበርቴዎች "ብድርና እርዳታ" ለማግኘት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች <u>የመዋቅር ማስተካከል ኘሮግራም</u> (Structural Adjustment Program) ተብሎ ይጠራል።

<u>የመዋቅር ማስተካከል ኘሮግራም በሦስተኛ ዓለም ሕዝቦች ላይ ያሳየውና/ የሚያሳየው ውጤት ምንድር ነው</u>?

ገበሬዎች ከጉርሳቸው የሚተርፈውን ምርት ገበያ አውጥተው መሸጥ አይችሉም። ከውጭ የሚገቡ የምግብ ሸቀጦች በጥራት፣ በብዛት እና በዋጋ ዝቅተኝነት አገር በቀሉን ይጥሉታልና። ስለሆነም ገበሬው ካሽ አግኝቶ ለማዳበሪያ ያወጣውን ወጪ ሸፍኖ፣ የመንግሥት ግብር ከፍሎ፣ የራሱን፣ የሚስቱንና የልጆቹን ልብስ ገዝቶ መዝለቅና መቀጠል ከማይችልበት ነጥብ ላይ ይደርሳል። ቤቱን ንብረቱን ጥሎ ላም በሬውን ሽጦ ይሰደዳል። ወደ ከተማ። ለልመና!

ድህው መማር፣ መታከም ... አይችልም። ከመንግሥት ስራ የሚባረርና ኑሮው የሚፈርሰው ሁልቆ መሳፍርት የሌለው ነው።

ግብርና እየተመናመነ ከሄደ፣ መንግሥት ብዙውን የተማረ ሰው መቅጠር የማይችል ከሆነ ጥያቄው ስራ ያለው አለ ወይ የሚለው እንጂ ስራ የሌለው ስንቱ ነው? የሚለው አይሆንም!!

ይህ ሁሉ የሚደረገው የእርዳታውንና የብድሩን ገንዘብ መመለስ እንዲቻል ነው!! የሚገኘው ብድርና እርዳታ የሕዝብን ተቃውሞ ለማፈን ለሚቋቋም የወታደር ኃይልና ለጦር መሳሪያ ነው። ዓለም አቀፉ ከበርቴ አገርን አራቁቶ እንዲገፍ ዘብ ለሚቆምለት ቡድን (መንግሥት) የሚከፈል ነው። አለም አቀፍ ከበርቴው ምድሩንም፣ ሀብቱንም ንግዱንም በእጁ እያስገባ የአገሩን ሕዝብ አገር የለሽ እያደረገው ነውና! በጣት የሚቆጠሩ የአገር ተወላጅ ቱጃሮችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች (የገገር መደቦች) እና ዓለም አቀፍ ከበርቴዎች የተሳሰሩበት ገመድ ነው።

ስለአዲሱ ዓለም አቀፍ የከበርቴ ስርዓት (globalization) ለመረዳት የሚፈልግ ሁሉ እጅግ ብዙ መጻሕፍት ገዝቶ ማንበብ ወይም ፈልጐ ማግኘት ይቻላል።

ይህንን አባባል አመሰካክር ለማመዛዘን፣ በዛሬ ጊዜ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካ፣ በደቡብ ምስራቅ እስያ፣ በላቲን አሜሪካ … ወዘተ አገሮችና በዓለም ተቆጣጣሪ መንግሥቶችና ከበርቴዎች መካከል የሚታየውን ቅራኔና ግንኙነት ዞር ብሎ ማየት ብቻ በቂ ነው። የዓለም አቀፍ ከበርቴዎች አገዛዝ በእያንዳንዱ የሦስተኛ ዓለም አገር ውስጥ የሚያካሂደው ገደብ የለሽ ብዝበዛና ቁጥጥር እውን ሊሆንና ቀጣይነት ሊኖረው የሚችለው አገር በቀል የሆኑ ታማኝ አሽከሮችና ቡድኖች ሲኖሩት ነው። በነዚህ ዓይነት ቡድኖች የሚመራ መንግሥት ተቋቁሞ በስልጣን ላይ ሲገኝ ነው። እነዚህ ዓይነት መንግሥቶች ሁሉንም የአገራቸው ሕዝብ መብትና ጥቅም ለዓለም አቀፍ ከበርቴ አገዛዝ አሳልፈው የሸጡ/የሚሸጡ ስለሆኑ ከባዕዳን ጌቶቻቸው ጋር የጥቅም ተካፋዮች እንደሆኑ/መሆናቸው ከማንም ሊሰወር የማይችል ነው። ለዓለም ተቆጣጣሪ ከበርቴዎች ስርዓት በሦስተኛው ዓለም ውስጥ የሚደግፉት "ዴሞክራሲ" ያልተገደበ ብዝበዛቸውን እውን የሚያደርግ አስተዳደር ብቻ ነው። አገርን አራቁቶ ሕዝብን አፍኖ የሚቆጣጠር የአምባገነኖች ስርዓት ብቻ ነው።

## ዓለም አቀፍ ከበርቴዎችና ተቃዋሚ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች

አብዛኛዎቹ ለቡድናቸው ስልጣን ብቻ የሚታገሉ ናቸው። ከወያኔ ጋር ያላቸው ልዩነት ከመንግሥት ሥልጣን ውጪ መሆናቸው ነው ማለት ይቻላል። በመሰረታዊ የፖለቲካ አመለካከታቸው ከወያኔ እጅግም የራቁ አይደሉም ለማለት ነው። ወያኔን ስልጣን ላይ ያወጡ ኃይሎችን ይወድዳሉ። ባለተራ ወያኔዎች እንዲሆኑም ዘወትር እነርሱን ይማፀናሉ/ደጅ ይጠናሉ።

እያንዳንዳቸው የተወሰነውን የሕዝብ ክፍል ብሔረሰብ እንወክላለን ስለሚሉ ከዚያ ውጪ ለሆነው ሕዝብ ጥቅምና መብት ለመታገል ዝግጁና ፈቃደኛ ሆነው አይታዩም። ስለሆነም ለሕዝቦች እኩልነትና ለአገር አንድነት (ለአንድነትና ለእኩልነት) ለሚደረገው ትግል ደንቃራና እንቅፋቶች እየሆኑ ናቸው።

በአንድነትና በእኩልነት መርህ ላይ የቆመ ሕብረ ብሔራዊ ድርጅት ተቋቁሞ እነዚህን ጠባብ ቡድኖች ማዳከም ካልተቻለ ያገር ውስጥና የዓለም አቀፍ የሕዝብ ጠላቶችን መታገልና ማሸነፍ እጅግ ከባድ ሊሆን ይችላል። በአንድነትና በእኩልነት መርህ ዙሪያ የአገሪቷን ሕዝብ ሁሉ ማሰለፍና ማታገል የሚችል ፖለቲካ ድርጅት መኖር/አለመኖር የሞት የሽረት ጥያቄ እየሆነ ቀርቧል።

በመጠኑም ቢሆን ከዚህ እይታና አመለካከት ጋር የተቀራረበ አቋምና መንፈስ ያለው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት ብቻ ነው። ወያኔ ተወግዶ በሕዝብ የፀደቀ ሕገ መንግሥት መርቀቅ አለበት። ይላልና። ለዚህም ይታገላልና።

ለኦነግና ከአገር ውጪ ለሚገኘው "የቅንጅት አመራር" ተብሎ ፀረ ሕዝብ የሆነውን አምባ ገነናዊውን የወያኔ ሕገ መንግሥት መሻር እንጂ መቀበል የለብንም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕብረትን አቋም (ከሌሎች ለይቶ) በሚገባ አጥርቶ የሚያውቅበት መንገድና ዕድል ካገኘ ሕብረትን መደገፉ እውቅ ነው። የራሱን መብትና ጥቅም ከመደገፍ የተለየ አይሆንምና።

በዚህም ምክንያት ነው ከመንግሥት ስልጣን ላይ ያለው ወያኔና ከመንግሥት ስልጣን ውጪ የሚገኙ ወያኔዎች የሕብረትን አቋም አጣመውና አወላግደው በማቅረብ ዘመቻ ላይ የተሰማሩት። ለዚህም ነው የሕብረትን አቋም ሽፋፍነውና አጥላልተው በጌቶቻቸው የሰማይ ፈረስ ላይ ሆነው ከታላቅ ወንድማቸው (ወያኔ) ጋር አዲስ አበባ ስብሰባ ለማድረግ የሚጣደፉት!!

በስም የወያኔ ተቃዋሚ/በተግባርና በእምነት
የወያኔ ደጋፊ የሆነ ሁሉ የአገርና የሕዝብ ጠላት ነው!

የሕዝብ ወዳጅና ጠላት ጐራ ይለይ!!

**በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት የድጋፍ ኮሚቴ**

7/6/2006